Government of Western Australia
North Metropolitan Health Service
Mental Health, Public Health and Dental Services

# ከጥርስ እጅግ ድንጋጤ በኋላ ምክር

ጉዳት የደረሰባቸው ጥርሶች ድንጋጤው ከተፈጠረበት በመቀጠል ለብዙ ወራት ወይም ለዓ መትም የሚሆን የተወሳሰበ በሽታ ችግር ሊፈጥር ይችል ይሆናል። ለተጎዱት ጥርሶች በተደጋ ጋሚ በጥርስ ባለሙያ መታየቱ አስፈላጊ ነው።

ለተጎዱት ጥርሶች እንክብካቤ ለማድረግ ወላጆች/ተንከባካቢዎች ጠቃሚ የሆነ ድርሻ ይጫወ ታሉ። መርዳት የሚችሉት:

- በጥርስ ባለሙያ የቀረበን ምክር በመከተል
- ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ በታቻለ መጠን በንጽህና ስለመጠበቁ በማረጋገጥ ይህም:
    - በቀን 2 x ጊዜ ቀስ አድርጎ ጥርስን መበረሽ
    - ለተመገቡ በኋላ ቦቅ ያለ ጨው ያለበት ውሃ አድርጎ አፍን ማጉመጥመጥ
- የሚከተሉትን ካስተዋሉ ለጥርስ ህክምና ክሊኒክ ማነጋገር:
    - ጉዳት በደረሰበት ጥርስ/ጥርሶች ላይ ማንኛውም የህብረ ቀለም ለውጥ። (ምስል/ቅርጽ/Figure 1)
    - ከተጎዳ ጥርስ ጋር የተዛመደ ማንኛውም ህመም ወይም እበጥ/ብጉር (ምስል/ቅርጽ/Figure 2)



**Figure 1:**
**የጠቆረ ጥርስ**



**Figure 2:**
**በሁለቱ የፊት ጥርሶች መካከል ማበጥ**

ለተጎዱ ጥርሶች ህክምና ብዛት ያለው ጉብኝት ሊያስፈልገው ይችላል። በዚህ ሊካተት የሚችለው:

- ለውተጎዳ ጥርስ እና አፍ በድንገተኛ ችግር ህክምና
- ስለመዳኑ ለማጣራት የራዲዮግራፍ
- “ለተሸረፈ ጥርስ” ለመጠገን ቀላል ሙሊት
- በጣም ለተጎዳ የሩት ካናል ህክምና ይሆናል።

ጉዳቱ ስለመዳኑ እና ለሚከሰት የተወሳሰበ ችግር ለመቆጣጠር በግምት በ3፤ 6፤ 12 እና 24 ወራት መካከል ባለው ጊዜ እንደገና ግምገማ ለማድረግ ቀጠሮዎች ሊያስፈልጉ ይችሉ ይሆናል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ልጅዎ በጉዳቱ በሚፈጠር የተወሳሰበ ችግር ምክንያት ለህክምና ወደ ልዩ ባለሙያ መላክ ሊያስፈልግ ይችላል። ወደ ልዩ ባለሙያ መላክ ካስፈለገ ለክፍያው የወላጆች/ተንከባካቢዎች ሃላፊነት ይሆናል።

ለማንኛውም ተጨማሪ መረጃ ሲያስፈልግዎ፤ እባክዎ ከዚህ በታች ባለ ክሊኒካል ቁጥር አድርጎም ማነጋገር ነው።

CLINIC STAMP

**ለበለጠ መረጃ እባክዎን ከእርስዎ ጥርስ ባለሙያ ጋር መነጋገር**

**የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ውቀውይም አስተያየት መስጠት ከፈለጉ?**
ይህ ሰነድ በሌላ አማራጭ የተለያየ ቅርጽ ሊቀርብ ይችላል፤ ይህም በጥያቄ በ braille, audio tape ወይም electronically ይሆናል.

Communications Officer, Dental Health Services
Locked Bag 15, Bentley Delivery Centre, WA 6983
(08) 9313 0555
publications@dental.health.wa.gov.au
**www.dental.wa.gov.au**

በዚህ ሰነድ የተጠቀሙት ማንኛውም ቅርጽ/ስእል ለመግለጫ ተብሎ ብቻ እንደሆነ ይህም ለአጠቃላይ መመሪያ ለማቅረብ ብቻ ነው።

CONSUMER REVIEWED
HealthyWA Health information for Western Australians

© 2020 Dental Health Services WA. All rights reserved.

DT37 v 09/22_Amharic